# የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ
# የጥቆማ አቀራረብ ሥርዓት

ሙስናና ብልሹ አሠራሮች በወቅቱ በሚገቱበት መንገድ ላይ ሥልታዊ በሆነና በተደራጀ መንገድ እንዲወገዱ ካልተደረጉ በቀር በአገር፣በህብረተሰብና በግለሰብ ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት መገመት ይቻላል፡፡

መንግሥትም የጉዳዮን አሳሳቢነት ከግምት ውስጥ በማስገባት የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን እንዲቋቋም ተደርጎ ውጤታማ የሆኑ ሥራዎች በመከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡

የተጀመረውን የፀረሙስና ትግል በተጠናከረ መልኩ ለማካሄድም በመንግሥት መ/ቤቶች ጥሩ ሥነምግባርን ለማስፈንና ሙስናን ለመከላከል የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ተደርጓል፡፡

እነዚህ በመወሰድ ላይ ያሉት እርምጃዎች ፍሬያማ ሊሆኑ የሚችሉት ህብረተሰቡና የመንግሥት ሠራተኞች የሙስና ድርጊቶችን " አያገባኝም" ብሎ ከማየት ባሻገር ነገ በራሳቸውም ላይ ሊደርስ እንደሚችልና በአገርም ላይ የሚያስከትለውን ችግር ከግንዛቤ በማስገባት ድርጊቶቹን በመጠቆምና በማጋለጥ ኃላፊነታቸውን መወጣት ሲችሉ ብቻ ነው፡፡

የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍሎችን ለማቋቋም መወጣው ደንብ ቁጥር 84/2003 መሰረት "ማንኛውም የሥራኃላፊ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ በመሥሪያ ቤቱ የሙስና ወንጀል ተፈጽሟል ወይም ሊፈፀም ይችላል ብሎ በሚጠረጥርበት ጊዜ ወዲያውኑ የማጋለጥ ግዴታ እንዳለበትና አለማጋለጥ አግባብ ባለው ህግ የሚያስጠይቅ መሆኑን፡፡ "

ይህን ኃላፊነት ለመወጣትና የሚቀርበውን ጥቆማ ውጤታማ ለማድረግ እንዲሁም ለአሠራርም አመቺ እንዲሆን ስም ገልጾ ወይም ሳይገለጽ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ጥቆማ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ጥቆማው የሚከተሉትን ነጥቦች አካቶ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

ሀ. የጠቋሚው ስምና አድራሻ (የግድ አይደለም)፤
ለ. የተፈጸመው ድርጊት ምን እንደሆነ፤
ሐ. ድርጊቱን ፈጸመ የተባለው ተጠርጣሪ ማንነት /ስም፣ ሙያ ወይም ሥራ አድራሻ ዕድሜና የሥራ መደቡን/
መ. ድርጊቱ የተፈጸመበት የሥራ ሂደት፤
ሠ. ድርጊቱ የተፈጸመበት ጊዜና ቦታ፤
ረ. በድርጊቱ የተጠቀሙ ሰዎች ወይም የተጎዱ ሰዎች፤
ሰ. በድርጊቱ የተገኘ ጥቅም መጠን የገንዘብ ግምት ወይም የደረሰ ጉዳት ግምት፣ ከድርጊቱ መፈጸም ጋር በተያያዘ የተደረገ ውል፣ ብድር ቀረጥ ወዘተ.
ሸ. የሚታወቅ ከሆነ የተገኘው ጥቅም የሚገኝበት ቦታ ወይም ሁኔታ፤
ቀ. የሚታወቅ ከሆነ በተጠርጣሪው ስም ያሉ ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች፤
በ. የጉዳዩን እውነተኝነት ሊያስረዱ የሚችሉ የሠነድ ማስረጃዎች የሚገኙበት ቦታ ወይም ጉዳዩን የሚያውቁ ሠራተኞች ወይም ምስክሮች ስምና አድራሻ፤

## የጥቆማ አድራሻዎች

በአካል መምጣት ለሚፈልጉ አሮጌው ፎቅ ቢሮ ቁጥር 26

ክፍሉ ባዘጋጀው የጥቆማ ሣጥኖች ውስጥ

046-220-94-05

ፖ.ሣ.ቁ. 32

ኢ-ሜይል፡- anti.corrup@ymail.com

ሙስናን በጋራ እንከላከል

ሙስናን መከላከል ልማትን ማፋጠን ነው